# በደቡብ ጎንደር ዞን ሦስት የትግራይ ተወላጆች መገደላቸው ተገለጸ

By **መርሻ ጥሩነህ** - 19/07/2021



በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን ፎገራ ወረዳ ሦስት የትግራይ ተወላጆች መገደላቸውን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን አስታወቀ፡፡
የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን(ኢሰመኮ) ለአዲስ ማለዳ በላከው መግለጫ ሐምሌ 4/2013 በአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን ፎገራ ወረዳ ልዩ ስሙ ወረታ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ፣ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ሦስት የትግራይ ተወላጆች በድንገት በተሰባሰቡ ነዋሪዎች በደረሰባቸው ድብደባ መገደላቸው ጥቆማ እንደደረሰው አስታውቋል፡፡

እንደ ኢሰመኮ ገለጻ፣ ጥቃቱ የደረሰው ከተጠቀሰው ቀን አስቀድሞ ፍየል ውኃ በሚባል ቦታ የህወሓት ኃይሎች በወሰዱት የጥቃት እርምጃ የፎገራ ወረዳ ነዋሪዎች የሆኑ የሚሊሽያ ቡድን አባላትና የወረዳው የሰላምና ጸጥታ ኃላፊ መገደላቸው ከተነገረ በኋላ ነው፡፡ ሐምሌ 4/2013 ረፋዱን የተገደሉት የወረዳው የሰላምና ጸጥታ ኃላፊ ትውልድ ቦታ ከሆነው ጕመራ ወንዝ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የኃላፊውን አሬሳ ለመቀበል የመጡ ነዋሪዎች ጥቃቱን እንዳደረሱ ነው የተገለጸው፡፡
የፎገራ ወረዳና የአካባቢው የጸጥታና የአስተዳደር ኃላፊዎች በወሰዱት አፋጣኝ እርምጃ ሁኔታው የተረጋጋና ተጨማሪ ጥቃት ሊፈጽሙ የነበሩ ስድስት ግለሰቦች በቁጥጥር ስር የዋሉ ቢሆንም፣ የተከሰተው ሁኔታ ወደ ሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች እንዳይዛመት ያሰጋል ብሏል ኢሰመኮ፡፡

ኢሰመኮ ለአዲስ ማለዳ በላከው መግለጫ "በሲቪል ሰዎች ላይ የሚደርስ እንግልት፣ ከሕግ አግባብ ውጪ የሆነ እስርና ጥቃት በአፋጣኝ ሊቆም ይገባል" ብሏል፡፡
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በትግራይ ክልል ከቀጠለው ግጭት ጋር ተያይዞ በሲቪል ሰዎች ላይ እንግልትና እስር፣ የንግድ ቤት መዘጋት፣ ብሎም በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት መከሰቱንና ሕይወት መጥፋቱን፣ እንዲሁም በታሳሪዎችና በምርኮኞች ላይ የሚደርስ ኢሰብአዊ አያያዝ፣ በስደተኞች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችና ሕጻናትን ለውትድርና መጠቀም የሚያመላክቱ መረጃዎች እጅግ አሳሳቢ ናቸው ብሏል፡፡

"በትግራይ ክልል በሚገኙ የኤርትራ ስደተኞችና ሲቪል ሰዎች ላይ በህወሓት ኃይሎች ተቃዋሚ ናቸው በሚል እየተወሰዱ ያሉት የግድያና የአፈና እርምጃዎች የሚያሳስቡ ናቸው፡፡ በአላማጣና አካባቢው በድጋሚ ባገረሸው ግጭትና በመኾኒ እየተወሰደ ስለመሆኑ በሚነገር የበቀል ጥቃት ከፍተኛ ቁጥር ያላው ሰው እየተፈናቀለ ነው" ሲል ስጋቱን ገልጿል ኢሰመኮ፡፡

ኢሰመኮ የግጭቱ መባባስና የግጭቱ ተጽእኖ በአፋርና በአማራ ክልል የሚገኙ ቦታዎችን ጨምሮ ወደ ትግራይ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ጭምር መስፋፋቱ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ጠቁሟል፡፡
እንዲሁም ኮሚሽኑ አዲስ አበባን ጨምሮ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል የሚደርሱትንና በትግራይ ተወላጆች ላይ የሚደርስ ከሕግ አግባብ ውጪ የሆነ እስር፣ የንግድ ቤት መዘጋት እና የእንግልት መረጃዎችንም እየተከታተለ መሆኑን ጠቁሟል፡፡
ከሰኔ 22/2013 ጀምሮ ተባብሶ የታየው ከሕግ አግባብ ውጪ የሆነ ክስተትና እስር ሁኔታ ተገቢውን ትኩረትና መፍትሔ ካለማግኘቱ በተጨማሪ፤ በስሩት የሚደመጡ የጥላቻና ግጭት ቀስቃሽ ንግግሮች ሁኔታው ሊያባብሱና ብሎም በማሕበረሰቦች መካከል ያለውን ትስስር ሊያላሉ የሚችሉ መሆኑን ኮሚሽኑ ጠቁሟል፡፡ በመሆኑም በየትኛውም አካባቢ ከሕግ

አግባብ ውጪ የታሰሩ ነዋሪዎች በአፋጣኝ ከእስር እንዲለቀቁና የፌዴራል መንግሥትም ሆነ የክልል መስተዳድሮች በነዚህ ነዋሪዎች ላይ እንግልት ያደረሱና ሌሎች ሕገ-ወጥ ድርጊቶች የፈጸሙ የሕግ አስከባሪ አካላትን ሕግ ፊት ሊያቀርቡ ይገባል ብሏል፡፡

በግጭቱ ለሚሳተፉ ወገኖች በሙሉ እንዲሁም የሚድያ ተቋማትን ጨምሮ ለአገራዊና ለዓለም አቀፍ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሙሉ ማንኛውንም የማኅበረሰብ ክፍል አደጋ ላይ ከሚጥል ንግግር፣ መግለጫዎችና ተግባራት እንዲቆጠቡ የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዳንኤል በቀለ(ዶ/ር) ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በትግራይ ክልል ቴሌኮሙኒኬሽንና ማኅበራዊ አገልግሎቶች መቋረጣቸው የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ሥራውን አዳጋች እንዳደረገበትም ጠቁሟል፡፡ ይሁን እንጅ ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ያለውን የተደራሽነት ሁኔታ በተመለከተ የሚያደርገውን ክትትል የሚቀጥልና በቆቦ፣ በወልዲያ እና በመርሳ ተጠልለው የሚገኙ ከአላማጣና አካባቢው የተፈናቀሉ ሰዎችን የሚጎበኝ መሆኑን ገልጿል፡፡

---

**ተጨማሪ ጽሑፎች፡**

- መንግሥት የዜጎችን ሕይወት ‹መታደግ› ለምን ተሳነው?
- የበረሃ አንበጣ አስከፊ ጉዳት ከአርሶ አደር ማሳ
- ለነዋሪዎቹ ገሀነም ሆኖ የኖረው ወልቃይት ጠገዴ

---

ቅጽ 3 ቁጥር 141 ሐምሌ 10 2013

**መርሻ ጥሩነህ**

*https://addismaleda.com*

## ስለ እኛ

አዲስ ማለዳ ወቅታዊ የአገራችንን ጉዳዮች በስፋትና በጥልቀት የምትተነትን፣ እንዲሁም የተረጋገጡና የትም ያልተሰሙ ዜናዎች የሚቀርቡባት የብዙኃን መገናኛ ናት፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚዲያ ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 241/2010 ተመዝግባለች፡፡

ያግኙን: info@addismaleda.com